# መርህ - ፖሊሲ

BOARD OF EDUCATION OF
MONTGOMERY COUNTY
የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ

**ተዛማጅ ግብአቶች፦** ABA, ABA-RC, ABC, BBB, CNA, CNA-RA, CNE, DDA-RA, DJA-RA, DJA-RB, ECN, FFA, FFA-RA, IGK-RC, JPG, KGA-RA

**ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት፦** School Support and Improvement; Chief Operating Officer

**ተዛማጅ ምንጮች፦** Annotated Code of Maryland, Business Regulation Article, Section 6-101; Criminal Law Article, Section 13-1803 and Section 13-1813

## ከትምህርት ቤት ጋር የተገናኘ የገንዘብ ማሰባሰብ - School-Related Fund-Raising

A. ዓላማ

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ውስጥ ወይም (MCPS)ን በመወከል ስለሚካሄዱ ከትምህርት ቤት ጋር ስለተገናኙ የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴዎች የማስተማሪያ ጊዜን ከማባከን ስለመጠበቅ፣ ስለ ተማሪዎች ደህንነት በከፍተኛ ደረጃ ጥንቃቄ ማድረግ፣ ለሁሉም ተማሪዎች የጋራ የትምህርት ቤት ተሞክሮዎችን የሚደግፍ፣ እና አግባብነት ያለው ኃላፊነት/ተጠያቂነትን የመዘርጋት ማእቀፍ ለመስጠት ነው።

B. ጉዳዩ

በትምህርት ቤቶች ወይም በት/ቤት ስፖንሰር በተደረጉ ቡድኖች ወይም በ MCPS ፋንታ በወላጅ እና በማህበረሰብ ቡድኖች አማካይነት የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴዎች የሚከናወኑት ከስቴቱ ሕግ እና ከ MCPS ህጎች ጋር በሚጣጣም መልኩ እና ለትምህርት ቤት አስተዋፆ የሚያደርግ ሲሆን የተማሪን ተሞክሮ የማስተማር ፕሮግራምን እና የሥራ ሒደትን እንዲሁም የተማሪዎችን ደህንነት አደጋ ላይ በማይጥል ሁኔታ መሆኑን እንደሚደግፍ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ-The Montgomery County Board of Education (Board) ፍላጎቱን ያረጋግጣል። የወላጅ እና የማህበረሰብ ቡድኖች የሚያካትቱት በዚህ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን፣ "Parent Teacher Associations (PTAs)፣ Parent Teacher Student Associations (PTSAs)፣ foundations፣ እና booster clubs" የተሰኙ አካላት ናቸው።

ቦርዱ እንደሚገነዘበው ገንዘብ ማሰባሰቡ ለማስተማር ተግባር ሳይሆን ለሌላ ዓላማ እና እነዚህ የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴዎች ለአጠቃላይ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባልነት ተሞክሮዎች አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

C. አቋም

1. ለትምህርት ቤቶች ስጦታ/እርዳታ ለመስጠት ወይም ገንዘብ ማሰባሰብ የሚፈልጉትን ከትምህርት ቤት ጋር ግንኙነት ያለው ገንዘብ የማሰባሰብ ጥረቶች የጋራ ዓላማን መሠረት ያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ከትምህርት ቤት አመራር ጋር እንዲተባበሩ የምናበረታታ ሲሆን፣ በዚህ ብቻ የሚወሰን ባይሆንም የሚከተሉትን የሚያካትት መሆን አለበት፦

   a) በትምህርት ቤት ስፖንሰር የሚደረጉ ቡድኖችን እንቅስቃሴዎች መደገፍ፣ በዚህ ብቻ የሚወሰን

ባይሆንም ማካተት ያለበት፣ በትምህርት ቤት የሚማሩ ክፍሎችን ወይም በየክፍል ደረጃ የሚገኙ ቡድኖችን፣ ክለቦችን፣ ቲሞችን፣ የስነጥበብ ሥራ የሚያካሄዱ ቡድኖችን፣ እና ካውንቲ አቀፍ የተማሪ ድርጅቶችን

b) ተማሪዎችን ለመጥቀም የሚረዱ እንቅስቃሴዎች

c) የ MCPS ፕሮግራሞችን ለማዳበር የሚረዱ የአማራጭ እንቅስቃሴዎችን ተጨማሪ ወጪዎች ለመሸፈን-ክፍያ መስጠት

d) ለግብረሠናይ ዓላማዎች ወይም የፋይናንስ ችግር ላለባቸው የማህበረሰብ አባላት ገንዘብ ማሰባሰብ እና እርዳታ-ስጦታዎችን ስለመሰብሰብ። ተማሪዎች በአካባቢያቸው እና የዓለምአቀፍ ማህበረሰ አባል መሆናቸውን የመረዳት እንቅስቃሴዎችን የሚያጎለብቱ የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴዎች የሚኖራቸውን አወንታዊነት - ዋጋ ቦርዱ ያረጋግጣል።

e) የማስተማር ፕሮግራምን የሚደግፉ ወይም የትምህርት ቤት አስተዳደራዊ ስራዎችን የሚደግፉ ተጨማሪ ማቴሪያሎችን-ቁሳቁሶችን ወይም የመስሪያ መሣሪያዎችን መስጠት

f) ለሠራተኞች በሙያ ማበልጸጊያ እንቅስቃሴዎች እንዲሣተፉ ተጨማሪ ድጋፍ መስጠት

2. ማናቸውም ተማሪዎች የሚሣተፉበት የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴ እና፣ በተለይም፣ ተማሪዎች በቀጥታ ከህዝብ ስለሚሰበስቡት ገንዘብ፣ የተማሪ ደህንነት እና ጤንነት ግምባርቀደም አሳሳቢ ጉዳይ ይሆናል።

3. ወላጅ ወይም የማህበረሰብ ቡድኖች፣ ወይም ተማሪዎች የማስተማር ፕሮግራምን ለማዳበር የተለዩ ፕሮግራሞችን ለመደገፍ ወይም ቁሳቁሶችን ለመግዛት ገንዘብ እንዲያሰባስቡ አይጠበቅም። ትምህርት ቤትን መሠረት ያደረገ የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴዎች ላይ መሣተፍ በራስ ፈቃደኝነት መሆን አለበት፣ እና ማንኛውም ተማሪ እንዲሳተፍ-እንድትሳተፍ ወይም ለማዋጣት መገደድ አይኖርበ(ባ)ትም።

4. ምንም እንኳን በርካታ ትምህርት ቤቶች እና PTAs/PTSAs ባለፉት ጊዜያት ገንዘብ ማሰባሰብ ላይ ተሰማርተው ቢሆንም፣ ገንዘብ ማሰባሰብ የእነርሱ ዋነኛ ትኩረታቸው አይደለም። በቦርድ ፖሊሲ - Board Policy ABC መሠረት፣ ስለ ወላጅ እና ቤተሰብ ተሳትፎ - Parent and Family Involvement ቦርዱ ከተማሪዎች ትምህርት ጋር የተያያዙ ሁለገብ-አጠቃላይ የቤተሰብ-ትምህርት ቤት አጋርነት፣ ስለ ወላጅ እና ቤተሰብ ተሳትፎ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች ሀገር አቀፍ መስፈርቶች መከበራቸውን ያረጋግጣል።

5. ማቴሪያሎችን እና የማስተማሪያ መሣሪያዎችን ለመግዛት የትምህርት ቤት ሠራተኞች በገንዘብ ማሰባሰብ-ፈንድሬዚንግ ላይ የሚደገፉ መሆን የለባቸውም።

6. እንደ ትምህርት ቤት አውደ ርእይ የመሣሰሉ አንዳንድ እንቅስቃሴዎች ለትምህርት ቤት ከሚረዱት ምንም ያህል የገንዘብ መጠን በተጨማሪ የወላጆችን ተሳትፎ የሚያዳብሩ እና የትምህርት ቤትን እና የማህበረሰብን ግንኙነት መንፈስ የሚያጎለብቱ ስለሆነ አስፈላጊ ናቸው።

7. በገንዘብ አሰባሳቢ ቡድኖች አማካይነት የተሰበሰበ ገንዘብ በመደበኛ የትምህርት ቀን የሚሠራ ማንኛውንም ሠራተኛ ለመቅጠር መጠቀሚያ ሊሆን አይችልም።

8. ቦርዱ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ውጪ ለካፒታል ኢንቨስትመንት ማሻሻያ የሚሆን ገንዘብን ስለመቀበል በቦርድ መርህ-Board Policy CNE መሠረት የአሠራር መመሪያ ይዘረጋል በሞንትጎመሪ ካውንቲ ገቢ ገንዘብ ያልተመደበላቸው የፋሲሊት ማሻሻያዎች - Facility Improvements That Are Not Funded With Montgomery County Revenues።

9. በቦርድ መርህ-Board Policy FFA መሠረት የትምህርት ቤት ፋሲሊቲዎችን ስያሜ ስለመስጠት ቦርዱ የአፈጻጸም ሒደት ያዘጋጃል፣ የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ ስያሜ - Naming School Facilities እና በግልጽ በቦርድ በተለይ ካልፀደቀ በስተቀር ገንዘብ ለማሰባሰብ ብቻ ሲባል ከፊል የትምህርት ቤት ፋሲሊቲ ስያሜን ይከለክላል።

10. በልግስና የሚሰጡ ነገሮችን ስለመቀበል እና ባጀት ሳይደለደል እቃዎችን እና የሥራ መሣሪያዎችን ስለመግዛት በ MCPS Regulation DJA-RB ደንብ መሠረት MCPS የአፈጻጸም ሥርአት ይዘረጋል፣ Purchase of Materials and Equipment Using Nonappropriated Funds and Acceptance of Donated Items።

11. የዚህ መርህ-ፖሊሲ አፈጻጸም ከ MCPS ጋር ጉድኝት/ተያያዥነት የሌላቸው ቡድኖች የ MCPS ፋሲሊቲዎችን ለሚጠቀሙ የጋራ ኤጀንሲዎች ቦርድ አማካይነት ለሚከናወን የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴ ተግባራዊ አይሆንም።

D. **ተፈላጊ ውጤቶች**

1. በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)፣ ትምህርት ቤት እና በትምህርት ቤት ስፖንሰር የሚደረጉ ቡድኖች፣ ወላጆች እና የማህበረሰብ ቡድኖች፣ የግል ድርጅቶች እና ፋውንዴሽኖች፣ ቢዝነሶች-የንግድ ድርጅቶች፣ እና የጋራ ዓላማ ላይ በሽርከና የሚሠሩ ግለሰቦች የጋራ ትብብርና ጥረት

2. ስለ ትምህርት ቤቶች እና ስለ ማህበረሰብ ፍላጎቶች እና ሪሶርሶች መረዳት እና ኮሙኒኬት ማድረግ

3. ስለ ፈንድሬዚንግ-የገንዘብ ማሰባሰብ እንቅስቃሴዎች ዓላማ፣ አፈጻጸም፣ እና ኃላፊነት/ተጠያቂነት ግልጽነት

E. **የትግበራ/አተገባበር ስልቶች**

የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ይህንን መርህ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆነ መመሪያ ወይም ሌላ አስተዳደራዊ ስርአቶችን ይዘረጋል-ትዘረጋለች።

F. **ግምገማ እና ሪፖርት**

ይህ ደንብ በቦርድ የድህረ እይታ መመርያ መሰረት ይገመገማል።

**የዚህ መርህ ታሪክ፡-** የፀደቀበት ውሳኔ ቁ. 311-89, May 22, 1989, amended by Resolution No. 404-12, September 11, 2012.